# ጋዳ ከፍ ያለው በኢፌዴሪ ህገመንግስት ነው

ኢብሳ ነመራ

የኦሮሞዎች ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ የአስተዳደር ስርአት ጋዳ ሰሞኑን በተባበሩት መንግስታት  የትምህርት፣ የሳይንሳና ባህል ድርጅት የማይጨበጡ ቅርሶች ኮሚቴ የዓለም ቅርስነት እውቅና ተየሰጠው መሆኑ ይታወሳል፤ አዲስ አበባ ላይ በተካሄደ 11ኛ የኮሚቴው ጉባኤ። ጋዳ ካሁን በኋላ የኦሮሞዎችና የኢትዮጵያውያን ቅርስ ብቻ አይደለም፤ የአፍሪካና የመላው ዓለም ጭምር እንጂ። የገዳ ስርአት የዓለም ቅርስ ሆኖ በመመዝገቡ አፍሪካውያን በሙሉ ተደስተዋል። ምዕራባውያን ራሳቸውን ብቻ የዴሞክራሲና የመልካም አስተዳደር ምንጭና መገኛ አድርገው የሚቆጥሩበትን ሁኔታ የቀየረ፣ አፍሪካውያንም ድንቅ የስልጣኔ ባለቤቶች መሆናቸውን ስለመሰከረ።

የጋዳ ስርአት ከሁለት አስርት ዓመታት በፊት ከኦሮሞዎችና ጥቂት በከፍተኛ ደረጃ የተማሩ ኢትዮጵያውያን ብቻ ነበር የሚታወቀው። አሁን ግን የሁሉም የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች አባላት ቢያንስ ነባር ሃገር በቀለ የኦሮሞዎች ዴሞክራሲያዊ የአስተዳደር ስርአት መሆኑን ግንዛቤ አላቸው። ይህ በኢፌዴሪ ህገመንግስት የተረጋገጠው የብሄሮች፣ በሄረሰቦችና ህዝቦች መብትና ነጻነት ውጤት ነው። ራሳቸውን በራሳቸው የማስተዳደር መብት የተጎናጸፉት የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች ታሪካቸውን የመንከባከብ ባህላቸውን የማጎለበትና የማስተዋወቅ መብታቸውም በህገመንግስት ተረጋግጧል። ይህ ህገመንግስታዊ መብት ጋዳ ከተሸሸገበት ለመላ ኢትዮጵያውያን ይፋ እንዲወጣ እድል ሰጥቶታል። የጋዳ በዩኔስኮ ለመመዝገበ መብቃት የኢፌዴሪ ህገመንግስት ውጤት ነው።

ጋዳ ሰሞኑን በዩኔስኮ የማይጨበጡ ክርሶች ኮሚቴ እውቀና ከማግኘቱ አስር ዓመታት አስቀድሞ በኢትዮጵያ ቅርስነት እውቅና አግኝቶ ተመዝግቦ ነበር። ልብ በሉ ገዳ ከ500 ዓመታት በላይ እድሜ ያስቆጠረ ስርአት ነው። በኢትዮጵያ ቅርስነት እውቅና የተሰጠው ግን ከአንድ ተኩል አስርት ዓመታት በፊት ነው። ባለፉት ስርአቶች ጋዳን ለማጥፋት ከፍተኛ ጥረት ሲደረግ ነው የቆየው። እናም ጋዳ የዩኔስኮን እውቅና ባገኘበት እለት አንድ አባ ጋዳ እንደተናገሩት የጋዳ ዓለም አቀፍ እውቅና ማግኘት ለኦሮሞ የዳግም ውልደት ያህል ነው።

ለመሆኑ ጋዳ ምንድነው? ጋዳ ለኦሮሞዎች ሁሉም ነገራቸው ነው። ጋዳ ይሄ ነው፣ ይሄ ነው ብዬ ከመናገር ይልቅ ኦሮሞዎች ጋዳን ተዉ ሲባሉ ተናገሩት የተባለውን ልጥቀስ፤ የጋዳን ምንነት በግልጥ ስለሚያሳይ። ኦሮሞዎች በንጉሰ ነገስቱ ዘመን ጋዳን ተዉ ይባላሉ አሉ። ይሄኔ፤ ጋዳን ትተን እንዴት ነው ቤተሰብ መስርተን የምናስተዳድረው? ልጅ ወልደን የምናሳድገው፣ አሳድገን የምንድረውስ እንዴት ነው? እንዴት ነው ከብት የምናረባው? እንዴት ነው አብረን የምንኖረው? ስንጣላስ የምንታረቀው እንዴት ነው? ከኦሮሞና ከሌሎች ብሄሮች ጎረቤቶቻችን ጋር እንዴት ነው አብረን የምንኖረው? ብንጋጭ እንዴት ነው የምንስማማው? ጠላት ሲመጣብን እንዴት ነው የምንከላከለው? ወዘተ የሚል ጥያቄ ነበር ያነሱት። ኦሮሞዎች ካለጋዳ መኖር አይችሉም ነበር። ጋዳ ሁሉም የኦሮሞዎች ማህባዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና አስተዳደራዊ ግንኙነቶችነ የሚዳኝ ስርአተ ነው።

ያም ሆነ ይህ ፊውዳላዊው ዘወዳዊ ስርአትና ሌሎችም ከውጭ የመጡ ሃይማኖቶችና አመለካከቶች ጋዳን ተጭነውት በአብዛኛው የኦሮሞ ህዝብ ዘንድ ከወሬ አልፎ የሚተገበርበት ሁኔታ አልነበረም። ጋዳ በቦረና፣ ጉጂ፣ በተወነ ደረጃ ደግሞ በቱለማ ኦሮሞዎች ዘንድ ብቻ ነበር የሚተገበረው። ጋዳ መልኩን ሳይለውጥ እዚህ እንዲደርስ ያደረጉት የቦረናና የጉጂ ኦሮሞዎች ናቸው። እርግጥ በቱለማ ኦሮሞዎች ዘንድም ተሸራርፎም ቢሆን ሲተገበር ቆይቷል፤ የቱለማ ኦሮሞ ማለት የሸዋ ኦሮሞ ጎሳዎችን ያጠቃልላል።

አሁን የጋዳ ምንነት ላይ የተግባባን ይመስለኛል። ስለጋዳ ይህን ያህል ከተግባባን የገዳ ስርአት ሁሉንም የህብረተሰብ ግንኙነት በስርአት የሚዳኝበትን አኳኋን ወደመመልከት እንሸጋጋር። ጋዳ ሁሉም ኦሮሞዎች - ከውልደት እስከ እርጅና ባለው እድሜ ውስጥ ያሉ ኦሮሞዎች ድርሻ የሚወስዱበት የአስተዳደር ስርአት ነው።

ጋዳ ሁሉም የማህበረሰብ አባል በየስምንት ዓመት በተከፋፋለ የእድሜ እርከን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ተሳትፎ የሚያደርጉበት የአስተዳዳርና የፖለቲካ  ስርአት ነው። በገዳ ውስጥ ከልደተ እስከ 80 ዓመት እድሜ ያላቸው ሰዎች የሚሳተፉበት 11  እርከኖች አሉ። እነዚህም። ከልደት እስከ 8 ዓመት Daa’imman ወይም Ittimakoo (ህጻናት)፣ ከ8 እስከ 16 ዓመት  Dabballee (የመጀመሪያ የልጅነት ደረጃ)፣ ከ17 እስከ 24 Foollee ወይም የወጣጥነት የእድሜ ደረጃ፣ ከ25 እስከ 32 ዓመት Raabaa/Kusaa (የአዋቂነት እድሜ)፣ ከ33 እስከ 40 ዓመት Raabaa/Dorii የጉልምስና እድሜ፣ ከ41 እስከ 48 Gadaa/Luuba (የሃላፊነት እደሜ) ሲሆኑ ከ49 እስከ 72 ያሉት በሶስት ተከፍለው ማለትም ከ49 እስከ 56፣ ከ57 እስከ 64 እና ከ65 እስከ 72 Yubaa (መምህራንና አማካሪዎች) ይሆናሉ። በመጨረሻም ከ72 እስከ 80 ዓመት እድሜ Gadammoojjii (የበላይ አማካሪ) ሲሆኑ ከ80 ዓመት በላይ Jarsasa (አዛውንት) ይባላል። የአዛውንትነት እድሜ የእረፍት ግዜ ነው።

በመቀጠል ለግንዛቤ ያህል በእያንዳንዱ በእያንዳንዱ የእደሜ እርከን ያለውን የስራ ድርሻና ሃላፊነት እንዲሁም የገዳን አስተዳደራዊ መዋቅር በመጠኑ እንመልከት።

ከለደት እስከ 8 ዓመት ያሉ ህጻናት የተካተቱበት ittimkoo በሚባለው መጀመሪያ የእድሜ አንጓ ውስጥ ያሉ ህጻናት ከምንም አይነት ሃላፊነት ነጻ ናቸው። Ittimkoo ወይም መቀላቀል የሚለው ቃል ህጻናቱ Waaqa ወይም እግዚአብሄር ከሰው ጋር የቀላቀላቸው መሆኑን ያመለክታል። እነዚህ ህጻናት የማህበረሰቡን መጪ እጣ ፈንታ የሚወስኑ ተስፋዎች ተደርገው ይወሰዳሉ። ህጻናቱ በ Waaqa (እግዚአብሄር) እና በሰው መሃከል እንዳሉ አገናኝ ድልድይ ተደርገው ይወሰዳሉ። በጋዳ ስርአት፣ መሰረት ህጻናት ላይ አካላዊ ቅጣት መፈጸም የተከለከለ ነው። የቤተሰቡ አባላት በሙሉ በተለይ እናቶቻቻው የሙገሳ መዝሙር እያዜሙ በእንክብካቤ ያሳድጓቸዋል።

Dabballee በሚባለው ከ8 እስከ 16 ዓመት ባለው የእድሜ ክልል የሚካተቱ ልጆችን በያዘው 2ኛው የእድሜ እርከን ላይ ልጆች ስም ይወጣላቸዋል። ከዚያ በፊት በሰውና በእግዚአብሄር መሃከል እንዳሉ ቅዱሳን የሚወሰዱት ህጻናት መጠሪያ ስም አይኖራቸውም። በዚህ እድሜ ላይ ያሉ ልጆች የሚሰየሙበት ስርአት Maqbaasaa (መቃባሳ) ይባላል። ይህ እድሜ የፈጣሪ ስጦታዎች የሆኑት ህጻናት ከቤተሰባቸው ወጥተው ከማህበረሰቡ ጋር የሚቀላቀሉበት በመሆኑ ልዩ ትርጉም ይሰጠዋል። በዚህ እድሜ ውስጥ የሚገኙ ልጆች የማህበረሰባቸውን ታሪክና ባህል እንዲሁም የመጀመሪያ ደረጃ ወታደራዊ ወይም የውጊያ ጥበብ እንዲለምዱ ይደረጋል። በዚህ እድሜ ያሉ ልጆች የዘር ሃረጋቸውን እንዲያጠኑ ይደረጋሉ። እንደእንቆቅልሽ አይነት Hibboo (ሂቦ) በተሰኘ ጨዋታ አእምሯቸውን ያዳብራሉ። Geerarsa (ጌረርሳ) የተሰኘውን ባህላዊ ጀግንነትን የሚያበረታታና ጀገኖችን የሚያሞግስ ዜማ ይለማመዳሉ። የኦሮሞ አማልክትን ያጠናሉ። ስነምግባርና ታሪክ ይማራሉ።

3ኛው እርከን ከ17 ስከ 24 ዓመት እድሜ ያሉ የሚካተቱበት ነው። ይህ የእድሜ እርከን foollee (ወጣትነት) ይባላል። ይህ እድሜ ወጣቶች የቤተሰብ ሃላፊነትን መሸከም የሚጀምሩበት እንዲሁም ወታደራዊ ወይም የውጊያ ጥበብ የሚሰለጥኑበት በመሆኑ ወሳኝ እድሜ ነው። የፈረስ ግልቢያና ጉግስ፣ ጦር ውርወራ የመሳሰሉትን የውጊያ ጥበቦች ይሰለጥናሉ። በዚህ እድሜ ያሉ ወጣቶች ለዘውትር ኑሮ የሚያስፈልጋቸውን የእርሻ መሳሪያን መስራትና የእርሻ ስራ፣ የከብት ርባታ ሞያ ይማራሉ። የማህበረሰባቸውን adaa (ባህል) seera (ስርአት/ህግ) በማስተዋል ስለቤተሰብ አስተዳደር ይማራሉ። በዚህ እድሜ ያሉ ወጣቶች እንዲሰሩና ለቀጣይ ህይወታቸው የሚያግዛቸው ጥሪት እንዲያፈሩ ይበረታታሉ። ወጣቶቹ ከዚህ በተጨማሪ በገዳ ሃላፊነት ላይ ላሉ ሰዎች ጥበቃ ያደርጋሉ። እንደአስፈላጊነቱ በ Abbaa duulaa/ አባዱላ ወይም የጦር ሚኒስትር አዝማችነት በውጊያዎች ላይ ሊሳተፉ ይችላሉ።

አራተኛውና ከ25 እስከ 32 ዓመት ያሉ የሚካተቱበት የእድሜ እርከን የሚገኙት ደግሞ kusaa/Raabaa ይባላሉ። ይህ የእድሜ ክልል የአዋቂነት እደሜ ነው። በዚህ እድሜ ክልል ያሉ ሰዎች ዋና ተግባር በአባ ዱላ ወይም በጦር ሚኒስትሩ አማካኝነት በሚሰጥ ትእዛዝ መሰረት ወታደራዊ አገልግሎት መሰጠት ነው። እርግጥ ቀደም ባለው የእድሜ እርከን ሳሉ የወሰዱትን ወታደራዊ ስልጠና አሁንም በአባ ዱላና በአንጋፋ ተዋጊዎች አማካኝነት በበለጠ ደረጃ መውሰዳቸውን ይቀጥላሉ። ከዚህ በተጓዳኝ የጋዳ አመራር ስርአት ስልጠና ይወስዳሉ። በዚህ የእድሜ እርከን የሚገኙ ሰዎች ሃገራቸውን በውትድርና የማገልገል ግዴታ ስለተጣለባቸውና እንደአጋጣሚ ውጊያ ላይ ቢሞቱ ቤተሰባቸው ስለሚበተን ትዳር መመስረትና ልጅ መውለድ አይፈቀድላቸውም። እርግጥ ሴቶች 24 ዓመት ሲሞላቸው ትዳር መመስረት ይፈቀድላቸዋል። ከጋብቻ በፊት ጾታዊ ግንኙነት ማድረግ የተከለከለ ነው።

አሁን ወደ ጋዳ አመራር ለመሸጋገር የሚያስችለውን 5ኛው የእድሜ እርከን ላይ ደርሰናል። ከ33 እስከ 40 ዓመት ያሉ ሰዎች የሚገኙበት ይህ የእድሜ እርከን Raabaa/Doorii ይባላል፤ አይን የሚገለጽበት የጉልምስና እድሜ እንደማለት መሆኑ ነው። እነዚህ ቀጣይ የጋዳ አመራረንት ቦታን የሚረከቡ ጎልማሶች የከፍተኛ ባለማእረግ ወታደሮች ናቸው። በዚህ እድሜ ላይ የፍልስፍና እና የከፈተኛ አመራር ክህሎት እንዲያገኙ የደረጋል። የግዜ አቆጣጠርና የስነክዋክብት እውቀት ትምህርት ይወስዳሉ። ይህ የእድሜ እርከን ወደ ጋዳ አመራርነት መሸጋጋሪያ ነው። በጋዳ አመራርነት ለመመረጥ በዚህና ቀደም ባለው የእድሜ እረከን የሚያስመዘግቡት ወጤት ወሳኝነት አለው። በ Raabaa/Dorii የእድሜ እርከን ያሉ ጎልማሶች የውሳኔ አሰጣጥ ላይ ድምጽ ባይኖራቸውም የገዳ ምክር ቤቶች ስብሰባዎች ላይ በመሳተፍ ልምድ እንዲቀስሙ ይደረጋል።

በዚህ የእድሜ እርከን ላይ የሚገኙ ጎልማሶች ትዳር የመመስረት ነጻነት ቢኖራቸውም የትውልድ ቅብበሎሹን ስለሚያዘባርቀው ልጆች እንዲወልዱ አይበረታቱም። በዚህ እድሜ ልጆች ቢወልዱ፣ ልጆቹ የከፍተኛ አመራር ምክር ቤቶች ውስጥ የመቀላቀል እድል አይኖራቸውም። ልጅ መውለድ የሚፈቀደው ሰዎች ልክ 40 ዓመት ሞልቷቸው የገዳ አስተዳደርን ለመረከብ በቅተው ሲመረቁ ነው። Ittimkoo የሚባሉት ህጻናት፣ Luuba/Gadaa የተሰኘው 6ኛው እርከን ላይ ደርሰው የጋዳ አመራርነትን የተረከቡ ሰዎች ልጆች ናቸው። የጋዳ ኡደት ይህን ተከትሎ ነው የሚከናወነው።

በጋዳ ስርአት ውስጥ ዋናው የእድሜ እርከን አምስቱን እርከኖቸ አልፈው በመመረቅ የሚደረስበትና ከ41 እስከ 49 ዓመት ያሉ ጎልማሶችን ያካተተው Luuba/Gadaa የተባለው 6ኛው እረከን ነው። በዚህ የእድሜ እርከን ሁሉንም ወታደራዊና አስተዳደራዊ ክህሎቶች በከፍተኛ ደረጃ በመካን ሃገርን የማስተዳደር የፖለቲካ ሃላፊነትን መረከብ የሚያስችል ብቃት ላይ የሚደረሰበት ነው። እዚህ እርከን ላይ የደረሱ ጎልማሶች በልዩ ስነስርአት ለስምንት አመታት ሃገር ለማስተዳደር የፖለቲካ ስልጣን ይረከባሉ። በዚህ የእድሜ እርከን ውስጥ የሚገኙ ጎልማሶች ቀደም ሲል ባለፉባቸው የጋዳ እርከኖች ባሳዩት ውጤታማነት ላይ በመመሰረት ለተለያዩ የሃላፊነት ቦታዎች ይመረጣሉ።

የጋዳ አስተዳደር የተለያዩ ተቋማት አሉት። ቀዳሚው ከ9 እስከ 12 የሚደርሱ አባላት ያለው የአስተዳደር ምክር ቤት ነው። ስራ አስፈፃሚው በBokkuu/ Abbaa gadaa ወይም ፕሬዝዳንት ይመራል። አስፈፃሚው ሁለት ምክትል ፕሬዝዳንቶችና የተለያዩ ዘርፎችን የሚመሩ ሚኒስትሮች አሉት። ስራ አስፈፃሚውና Bokkuu (ፕሬዝዳንቱ) የአገልግሎት ዘመናቸውን በጨረሱ አባገዳዎችም የምክር አገልግሎት ያገኛል። ፕሬዝዳንቱ ጦርነት የማወጅ፣ የሰላም ስምምነት የመፈጸም፣ እርቅ የመዋዋል ስልጣን አለው።

የጋዳ ስርአት Caffee (ጨፌ) በመባል የሚታወቅ ፓርላማ አለው። ፓርላማው በጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚመራ ሲሆን ህግ የማውጣት ስልጣን አለው። Abbaa dubbii ወይም የፓርላማው አፈጉባኤ ፓርላማው ያወጣውn ህግ ለህዝብ የለፍፋል። የጋዳ ስርአት ህግ ተርጓሚ በ Abbaa alangaa (አባ አለንጋ) ይመራል። ህግ ተርጓሚው በፓርላማ የጸደቁ ህጎችን ያስከበራል።

በዚህ በ6ኛው እርከን ላይ ከሚገኘውና የፖለቲካ ስልጣንን ከተረከበው ትውልድ ቀጥሎ በ7ኛ፣ 8ኛና 9ኛ የእድሜ እርከን ላይ Yubaa (ዩባ) የሚባሉ ከ49 እስከ 56፣ ከ57 እስከ 64 እና ከ65 እስከ 72 ዓመት እድሜ ክልል ያሉ አዛውንቶች የተካተቱባቸው ሶስት ቡድኖች አሉ። የዩባ ቡደኖች የአመራር ግዜያቸውን ጨርሰው ስልጣን ያስረከቡ ልምድ ያላቸው በሳል ሰዎች የተካተቱበት ነው። ዩባዎች በሃላፊነት ላይ ላለው አመራር የማማከር አገልግሎት ይሰጣጡሉ።

በገዳ ስርአት በስራ ላይ ያለው የመጨረሻው እርከን ከ72 እስከ 80 ዓመት እድሜ ክልል ያሉ የካበተ ልምድ ያላቸው አዋቂዎች የተካተቱበት Gadammoojjii (ገደሞጂ) የሚባለው እርከን ነው። በዚህ እስድሜ ላይ ያሉ የበቁ አዛውንት በአንጋፋ አማካሪነት፣ እንዲሁም ባህላዊና ማህበራዊ ሁነቶችን በመምራት ያገለግላሉ። ከ80 ዓመት እድሜ በኋላ እረፍት ነው። በዚህ እድሜ ክልል ያሉ አዛውንት Jaarsa (ጃርሳ) ይባላሉ። ልዩ እንክብካቤ ያደርግላቸዋል። አዛውንቱ ሁሉም የማህበረሰቡ አባላት ልክ Ittimkkoo እንደሚሰኙት ከልደት እስከ 8 ዓመት እድሜ ያላቸው ህጻናት ቅዱስ ተደርገው ይወሰዳሉ። ህጻናቱ ከእግዚአብሄር (Waaqa) የተላኩ አዛውንቱም ወደእግዚአብሄር ለመሄድ የተዘጋጁ ስለሆኑ ነው እንደቅዱስ የሚታዩት።

እንግዲህ ዩኔስኮ  በዓለም የማይጨበጡ ቅርስነት የመዘገበው የጋዳ ስርአት በአጭሩ ይህን ይመስላል። ጋዳ ለዚህ እንዲበቃ ያደረገው የኢፌዴሪ ህገመንግስት ነው። ጋዳ አሁን የኦሮሞዎች ብቻ ሳይሆን የዓለም ሃብት ነው፤ እንደ የሰው ልጅ ስልጣኔ መገለጫ ነው የሚታየው። እናም የጋዳ ስርአትን የበለጠ በማጥናትና ለዓለም በማስተዋወቅ ለገጽታ ግንባታና ለቱሪዝም መስህብነት መጠቀም ይኖርብናል። የዚህ የዳበረ ስርአት ባለቤት በመሆናችን ልንኮራ ይገባል።